በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# ቅድስት ሥላሴ - ክፍል 2

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com

***<u>ቦታ፡-</u>*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ነሐሴ ፳፯ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# እግዚአብሔር ወልድ

- እግዚአብሔርን መርምረን ለማወቅ ያለመቻላችን ችግር ጉንዳን ሰውን ለማወቅ የገጠማት ዓይነት ችግር ነው፡፡ ለጉንዳን ዓይኖች ሰው በሁሉ ቦታ የሚገኝ ይሆንባታል፡፡ ጉንዳን በዕድሜዋና በችሎታዋም ሁሉ ተጠቅማ የሰውን ምንነት ሙሉ ለሙሉ ለማወቅ ያዳግታታል፡፡ በአንጻሩ ሰውም ራሱን ለጉንዳን ሊገልጥ ወይም ሊያስረዳ የሚችልበት መንገድ እስካሁን አላገኘም፡፡ እንዴት ያለ አሳዛኝ ነገር ነው!
- ሁለቱ ሊተዋወቁ የሚችሉበት አንድ ብቸኛ መንገድ ቢኖር ጉንዳን ሰው ሆና ስለሰው ማንነት ማወቅና ሰውም ጉንዳን ሆኖ ስለጉንዳን በጥልቀት መረዳት ነው፡፡ የሚያሳዝነው ግን ሁለቱም ይህንን አሳዛኝ ነገር መፍታት አለመቻላቸው ነው፡፡ በዚህ የተነሳ የሰውም የጉንዳንም ችግር ለዘላለም ይቀጥላል፡፡
- እግዚአብሔርንም የማወቅ ነገር እንዲሁ ሊሆን ይችላል፡፡ ሰው በጠባብ አእምሮው ሊኖር የሚችለውን የችሎታውን ድንበር አልፎ እግዚአብሔርን ሊያውቅም ሆነ ሊያይ አይችልም፡፡
- ወደ እውነተኛው የወይን ዛፍ ምሳሌ ስንመለስ ዛፍ በመሬት ውስጥ ሆኖ በማይታየው ሥሩ ሲኖር የሥሩን መኖር ግን ሳናውቅ ወይም ሳንረዳ ወይም የሥሩን ጥልቅ መለያ ምልክት ለይተን ለማወቅ ያለመቻል ዕድል ሊኖር እንደሚችል ባለመዘንጋት ነው፡፡ ይህም ስለ ዛፍ የዕውቀት እጥረት ያለብን መሆኑ ማሳያ ነው፡፡
- የወይኑን ዛፍ መኖሩን ከነመለያ ማንነቱ ለማወቅ ከሥሩ በተጨማሪ አንድ ነገር ያስፈልገናል፡፡ ዛፉ ራሱን ገልጾ ማስረዳት መቻል አለበት፡፡
- ቅጠሎቹንና ፍሬዎቹን የያዙትን ቅርንጫፎች ወይም በሌላ ቋንቋ የዛፉን ምስል ማየት ያስፈልገናል፡፡ እነዚህን ማየት ከቻልን ዛፉን እያየሁ ነው፣ ዛፉ ይኸውና፣ ይህንና ይህን የመሰሉም መለያ ምልክቶች አሉት ማለት እንችላለን፡፡

# <u>እግዚአብሔር ወልድ</u>

- እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት መንገድም የወይን ዛፉን የመሰለ ነው፡፡ እግዚአብሔር እንደ ወይን ዛፍ ሥር የማይታይ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ይህን ሲያረጋግጥልን "እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው።" ***<u>ቆላ 1፡15፡፡</u>*** **ብሎናል፡፡**
- **በአንድ ቦታ ብቻ ሊገኝ ከሚችለው ከወይኑ ዛፍ ሥር በተለየ መልኩ እግዚአብሔር በሁሉም ሥፍራ ያለና የሚኖር ምሉዕ በኩለሄ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለነቢዩ ለኤርምያስ** "ሰው በስውር ቢሸሸግ፥ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን? " ***<u>ኤር 23፡24፡፡</u>*** **እንዳለው፡፡**
- **ልበ አምላክ ዳዊትም በመዝሙሩ** "ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ፥ አንተ በዚያ አለህ። ወደ ሲኦልም ብወርድ፥ በዚያ አለህ። እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ፥ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር፥ በዚያ እጅህ ትመራኛለች፥ ቀኝህም ትይዘኛለች።" ***<u>መዝ 138፡7-10፡፡</u>*** **ብሎ በአድናቆት እንደዘመረለት እግዚአብሔር ምሉዕ በኩለሄ ነው፡፡**
- **ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ እንደተናገረው** "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤" ***<u>ዮሐ 1፡18፡፡</u>***
- **እግዚአብሔር ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፡፡** "እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም፡፡" ***<u>ቀዳ ጢሞ 6፡16፡፡</u>***
- እግዚአብሔር ሙሴንም "ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም።" **ብሎታል፡፡** ***<u>ዘጸአ 33፡20፡፡</u>***

# እግዚአብሔር ወልድ

- እነዚህን እውነታዎች መሠረት አድርገን የተወሰንን የሆን እኛ የማይወሰነውን ምሉዕ በኩለሄ እና የማይታይ የሆነውን እግዚአብሔርን እንዴት ልናውቀው እንችላለን? እግዚአብሔርን ልናውቀው እስከፈለግን ድረስ ይህ ጥያቄ ይኖራል፡፡
- ለጥያቄያችንም  መልስ ካላገኘን  ስለእግዚአብሔር ሰው መሆን  ደግሞ ለመረዳት ሌላ ችግር ይገጥመናል፡፡ ይህ ችግር ምናልባትም እግዚአብሔር ራሱን ሊገልጥልን አልቻለም ወይም አምላክ አይደለም ወይም የለም ወደ ማለትም ሊያደርሰን ይችል ይሆናል፡፡
- የወይን ዛፍ ራሱን በቅርንጫፎቹ ወይም በሥዕሉ መግለጥ እንደቻለ ሁሉ እግዚአብሔርም ለፍጥረታቱ ራሱን የሚገልጥበት መንገድ አለውና እግዚአብሔርን አመስግኑት፡፡
- ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ “መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።” ***ዮሐ 1፡18*** **በማለት  ስለ**ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልናል፡፡
- **አባቱ የተባለው እግዚአብሔር አብ ሲሆን አንድ ልጁ የተባለው እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡**
- **በአባትና ልጅ መካከል ያለው ግኑኙነት በዛፉና በሥሩ መካከል እንዳለ ግኑኙነት ነው፡፡**
- **ግንዱ ከሥሩ የተገኘ ሲሆን ከሥሩም ሳይለይ ይኖራል፡፡**
- ዛፉ ሕይወት ያለው ዛፍ እንዲሆን በግንዱና በሥሩም መካከል የማያቋርጥ ግኑኝነት ሊኖር ያስፈልጋል፡፡

# እግዚአብሔር ወልድ

- እንዲሁ እግዚአብሔር ወልድ ከአባቱ ሳይለይ ተወለደ፡፡ ጌታችን "አብ በእኔ እንደ ሆነ እኔም በአብ እንደ ሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ።" ***ዮሐ 10፡30፡፡*** እንዳለ፡፡
- **የወይኑ ዛፍ ግንድ ከሥሩ ጋር አንድ ነው፡፡** እግዚአብሔር ወልድ ከአባቱ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እንዲሁ አንድ ነው፡፡ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እኔና አብ አንድ ነን።" **ዮሐ 10፡30፡፡ እንዳለ፡፡**
- **የወይኑ ዛፍ ግንድ ወይም ሥዕሉ ተፈጥሮውንና ኀልውናውን ያስረዳል፡፡ ግንዱንና በላዩ የሚገኙትን የተሸከማቸውን ቅርንጫፎች፣ ቅጠሎችና ፍሬዎች ተመልክተንም እዚህ ጋር ዛፍ አለ ልንል እንችላለን፡፡ እንዲሁ ልጁ** እግዚአብሔር ወልድ የእግዚአብሔርን ኀልው ሆኖ መኖርና የብቻው የሆነውን ባሕርይውን ይገልጣል፡፡ ጌታችን ለፊሊጶስ "ፊልጶስ። ጌታ ሆይ፥ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው። ኢየሱስም አለው፡- አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴትስ አንተ። አብን አሳየን ትላለህ?" ***ዮሐ 14፡8-9፡፡*** **እንዳለው፡፡**
- "ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በሚታመን ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል።" ***ቀዳ ዮሐ 4፡15፡፡***
- "ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም። የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።" ***ቀዳ ዮሐ 5፡12-13፡፡***
- "ከእግዚአብሔር አብና ከአብ ልጅ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ምሕረት ሰላምም በእውነትና በፍቅር ከእኛ ጋር ይሆናሉ።" ***ቀዳ ዮሐ 1፡3፡፡***

# <u>እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ሕያው ቃል ነው</u>

- ወልድ (ልጁ) “የእግዚአብሔር ቃል” ይባላል፡፡ ቃል ለመግባባት መሠረት ነው፡፡ እግዚአብሔር የተናገረን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው፡፡ እግዚአብሔር ስለ ራሱ ልገልጥልን ሊነግረን የወደደው ሁሉ የተገለጠልን በአምላካችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡
- አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *ሥጋ* የለበሰ ሕያዋ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ለቅዱስ ፊሊጶስ “እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፤ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ *ሥ*ራውን ይሠራል።” ***<u>ዮሐ 14፡10፡፡</u>*** “ስለዚህም ኢየሱስ፦ የሰውን ልጅ ከፍ ከፍ ባደረጋችሁት ጊዜ እኔ እሆን ዘንድ አባቴም እንዳስተማረኝ እነዚህን እናገር ዘንድ እንጂ ከራሴ አንዳች እንዳላደርግ በዚያን ጊዜ ታውቃላችሁ።” ***<u>ዮሐ 8፡28፡፡</u>***
- አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ሰላምና ይቅርታ መልእክት ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ “መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ ሰላምን፥ ቀርበው ለነበሩትም ሰላምን የምስራች ብሎ ሰበከ፤ በእርሱ *ሥ*ራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና።” ***<u>ኤፌ 2፡7-18፡፡</u>***
- **ኖኅ የላካት ርግብ የለመለመ የወይራ ቅጠል ይዛ ስትመለስ** “ኖኅም ከምድር ላይ ውኃ እንደ ቀለለ አወቀ።” ***<u>ዘፍጥ 8፡11፡፡</u>*** **ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኖኅና ቤተ ሰቡም መረጋጋትን አግኝተዋል፡፡**
- እንደዚሁ ሁሉ ክርስቶስም የእግዚአብሔር ሕያው መልእክት ሆኖ የአዲስ ኪዳንን - የምሕረት ዘመንን መምጣት አብስሯል፡፡ ኀርፉ - የጨለማው ዘመን ማለፉን የአዲሱ ቃል ኪዳን መልእክት ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ወልድ ነው፡፡

# ወልድ - ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ የተገለጠ እግዚአብሔር ነው

- የዛፍ ምስል የዛፉን ምንነት የሚገልጥ ነው፡፡ በሥዕል ላይ የምናገኘውም ዛፍ ቅደም ተከተል ባለው ሁኔታ ስለ ራሱ ያስረዳናል፡፡
- ኢየሱስ ክርስቶስ “**የእግዚአብሔር ቃል**” **ነው ስንል እግዚአብሔር ልንረዳው በምንችልበት ግልጽ መንገድ ራሱን በልጁ (በእግዚአብሔር ወልድ - ኢየሱስ ክርስቶስ፣ አማኑኤል፣ መድኃኔዓለም) በኩል ገልጦልናል ማለታችን ነው፡፡**
- **ቅደም ተከተሉን በጠበቀ መልኩ ስለ እግዚአብሔር የምናስረዳበት እርሱ ቀል - ልጁ (እግዚአብሔር ወልድ - ኢየሱስ ክርስቶስ፣ አማኑኤል፣ መድኃኔዓለም) ነው፡፡**
- **ቅዱስ ጳውሎስ ይህን እውነት በተለያዩ መንገዶች በሚከተለው መልኩ ገልጦታል፡፡**
    - **ክርስቶስ** “እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው።” **ቆላ 1፡15፡፡**
    - **ክርስቶስ** “ልጁ የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ፥ ሁሉን በስልጣኑ ቃል እየደገፈ፥ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ፡፡” **ዕብ 1፡3፡፡**
- **ቅዱስ ዮሐንስም፡-**
    - “የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ መጣ፥ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው።” **ቀዳ ዮሐ 5፡20፡፡**
    - “ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው።” **ቀዳ ዮሐ 1፡3፡፡**
- **የኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርልጅነት የእጊዚአብሔርን ሰው ሆኖ መገለጥ የሚያስረዳ ነው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስም** “መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።” **ዮሐ 1፡18፣ ቅዱስ ጳውሎስም** “ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤” **ገላ 4፡4፡፡ እንዳሉ፡፡**

# <u>እግዚአብሔር ወልድ - ኢየሱስ ክርስቶስ</u>

***<u>ማጠቃለያ</u>***

- ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስንናገር የምንናገረው ሰማይና ምድርን ፈጥሮ ሰው በመሆን ራሱን ስለገለጠው እግዚአብሔር ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተገለጠ እግዚአብሔር ነውና፡፡ "እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤ በሥጋ የተገለጠ፥ በመንፈስ የጸደቀ፥ ለመላእክት የታየ፥ በአሕዛብ የተሰበከ፥ በዓለም የታመነ፥ በክብር ያረገ።" **ቀዳ ጢሞ 3:16፡፡**
- **እግዚአብሔር የተገለጠው በልጁ - በቃሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ *<u>የሐ ሥራ 2:22፣ ሮሜ 1:3-4፣ ቲቶ 3:4፣ ቀዳ ዮሐ 1:2፡፡</u>***
- **ልጁን (ወልድን) - ኢየሱስ ክርስቶስን ማመን ራሱን የገለጠውን እግዚአብሔርን ማመን ነው፡፡**
- **በልጁ (ወልድ) እግዚአብሔርን አውቀነዋል፡፡**
- **እግዚአብሔር ራሱን ገልጦልናልፈቃዱንም በቃሉ (በወልድ - ኢየሱስ፣ ክርስቶስ፣ መድኃኔዓለም፣ አማኑኤል) በኩል አውቀናል፡፡**
- **በእግዚአብሔር ልጅ ማመን ማለት አንዱ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ በሥጋ ማርያም እንደተገለጠ ማመን ነው፡፡**
- "በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም። … በዓለም ነበረ፥ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፥ ዓለሙም አላወቀውም። የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን።" ***<u>ዮሐ 1:1-14፡፡</u>***

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org